# ግራ ቀኙን እዩ

ገና በጠዋት ï በማለዳው
በአፍላ ï ዕድሜው
የወገን እሮሮ የሰማ
በሕዝብ ጭቆና ï ልቡ የደማ
ለሀገር ክብር ï ለወገን ነፃነት
አጥንቱን ሊገብር ï
ደሙን ሊያፈስለት
ስንቱን ተራራ ወጣው
ስንቱን ሸለቆ ተሻገረው
ይናገር በርሃው ï
ያንጎራጉር ጫካው
ወንዙም ይቃኝለት ï
ይዘምር ተራራው
እነደ አክሱም ሀውልት ï
እነደ ላሊበላ
በቃሉ የፀና ï
ማተቡን ያልበላ

ያን ቆራጥ ፋኖ
መች ሞተና ï ሞተ ትላላችሁ
መለስ በሉ እዩ ï ታገኙታላችሀ
ግራ ቀኙን እዩ ï ታገኙታላችሁ !

የጭቁን ሕዝቦች ጠበቃ
ወሰላመ ቋንቋ
የችጋርን ቆሌ ያስደነበረ
የኋላ ቀርነትን ï
ቀንበር የሰበረ

ያን ጀግና ታጋይ
እንዴት ሞተ ትላላችሁ
መለስ በሉ እዩ ï ታገኙታላችሁ
ግራ ቀኙን እዩ ï ታገኙታላችሁ!

እነደ ሻማ እየበራ
በድንቁርና ላይ ፈንጥቆ ጮራ
ብሩሁን ዘመን የገለፀ
በራስ መተማመንን ያሰረፀ
መጭውን ትውልድ የቀረፀ

መቼ አለፈና ï የለውጥ ሐዋርያው
ትላንት አሀድ ነበር ï
ዛሬማ እልፍ ነው!
የኢትዮጵያ ህዳሴ ï
ሕያው ሐውልቱ ነው!

ታዲያ ስለምን ጀግናን ï
ሞተ ትላላችሁ
መለስ በሉ እዩ ï ታገኙታላችሁ
ግራ ቀኙን እዩ ï ታገኙታላችሁ!

ዘላለም ይብዛወርቅ ፡ ለንደን ፡ ነሐሴ 2004